# ከወታደራዊ ግዳጅ ባሻገር

**ግርማ መ. 01/23/13**

የዚህ ፅሁፍ መነሻ በሀገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ ከየካቲት 1 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ ለአንድ ሳምንት የሚከበረውን የመከላከያ ሰራዊት ቀን ምክንያት በማድረግ ጥር 2 እና 3/2005 ዓ.ም ‛ህገመንግስታዊ ታማኝነታችንና ህዝባዊ ባህሪያችን እንደተጠበቀ ይኖራል!!´ በሚል መሪ ቃል የአገር መከላከያ ሚኒስቴር በአገሪቱ የተለያዩ ሚዲያዎች ውስጥ ለሚሰሩ ጋዜጠኞች ባዘጋጀው የጉብኝት ፕሮግራም ላይ መገኘቴ ነው።

ጉብኝቱ የተካሄደው በአዲስ አበባ (በመከላከያ ሎጂስቲክስ መምሪያና ስታፍ ኮሌጅ) እና በቢሾፍቱ (መከላከያ ኢንጂነሪንግ ኮሌጅ፣ አየር ኃይል፣ ደጀን አቪየሽንና ቢሾፍቱ ኦቶሞቲቪ ኢንጂነሪንግ ማዕከል) ሲሆን ይህ ጽሁፍ በተለይ የሎጂስቲክ መምሪያውንና የቢሾፍቱ ኦቶሞቲቪ ኢንጂነሪንግ ማዕከልን የስራ እንቅስቃሴዎችን በጥቂቱ ለመቃኘት ይሞክራል፡፡

የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት በመደበኛ መጠሪያ ስሙ ‛የሀገር መከላከያ ሰራዊት´ የአገር አለኝታነቱን ያስመሰከረ የመልካም ታሪክ ባለቤት ስለመሆኑ ማስረጃ ማፈላለግ አያሻም። በአገሪቱ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ህዝባዊነትን በተላበሰ መልኩ የተዋቀረው የአገሪቱ ብሄራዊ መከላከያ ኃይል ህያው ገድሎቹ፣ አይበገሬነቱ፣ ተወዳዳሪ የለሽ ጀግንነቱ የታሪኩ ገፅታዎች ናቸው። የአገራችን መከላከያ ሰራዊት በትእቢት ያበጡ የውጭ ወራሪ ኃይሎችን በጀግንነት ከመመከት ባሻገር የአገሪቱን የልማት፣ የሰላምና የዴሞክራሲ ግንባታ ሂደት በተግባር በማገዝ እያበረከተ ያለው አስተዋፅኦም የማንነቱ መገለጫዎች መሆን ከጀመሩ ሁለት አስርት ዓመታት እድሜን አስቆጥሯል፡፡

ይህ ብቻም አይደለም፤ ሰራዊታችን ሰላም በደፈረሰበት፣ ግጭት በተፈጠረበት፣ ህዝቦች ባልተፈለጉ ጦርነቶች በተሰቃዩበት፣ ሽብርተኝነት በተንሰራፋባቸው የአፍሪካ አገራት ሁሉ - - - ሰላም አስከባሪነትን ያህል ከባድ ሀላፊነት በመሸከም የተጣለበትን ወታደራዊ፤ አገራዊና አህጉራዊ ግዳጆች በብቃትና በአስተማማኝነት የተወጣ ሰራዊት ነው። በዚሁ አኩሪ ወታደራዊ ብቃቱና ሰላም ማስከበር ተገበሩ ከአለም የመከላከያ ሰራዊት ተቋማት መካከል

በአራተኝነት፣ ከአፍሪካ ደግሞ በአንደኝነት ደረጃ ላይ በመቀመጥ ስሙ በወርቅ ቀለም ሊሰፍርና በተባበሩት መንግስታት የሰላም ማስከበር ተቋም በኩል ሙሉ ዕውቅናን ለማግኘት የቻለ ከኢትዮጵያ አልፎ የአፍሪካ ደጀን ለመሆን የበቃ ሰራዊት ነው። ይህም ዕውነታ በተለያዩ ዓለም አቀፍ መድረኮች ላይ በይፋ የተነገረ ከመሆኑም በላይ በሌሎች በርካታ ሰነዶች ላይም በስፋት ሰፍሮ ይገኛል።

ወደጉብኝቴና በጉብኝቴ ወቅት ስላየሁት፣ ስለተረዳሁተና ከሁሉም በላይ እጅግ ስለተደነቅሁባቸው የሰራዊታችን ሌላ ገፅታዎች በመመለስ ጥቂት ልበል።

ሀሙስ (2/5/2005 ዓ.ም)፣ 4"00 አካባቢ ተጋባዥ ጋዜጠኞች ሁሉም በመከላከያ ሰራዊት መኮንኖች ክበብ ቅጥር ጊቢ ውስጥ ተገኝተናል። 5"00 አካባቢ ወደ አዳራሽ እንገባ ዘንድ በአስተናባሪ መኮንኖቹ ተጋብዘን፤ ገባን። በኢንዶክትሪኔሽን መምሪያ ሀላፊው ብ/ጀነራል ገ/ ኪዳን ገ/ ማሪያም ሰፊ ማብራሪያና ዝርዝር ፕሮግራም ገለጻና በመኮንኖች ክበብ አዳራሽ ውስጥ የመልካም ምሳ መስተንገዶ ተደርጎልን ወደ መጀመሪያው የጉብኝት ስፍራ በተዘጋጁልን ዘመናዊ ኮስትሮች ተጓዝን፤ ወደ ሎጂስቲክስ መምሪያ - አዲስ አበባ ስድስት ኪሎ።

የሎጂስቲክስ መምሪያ በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ውስጥ ካሉት መምሪያዎች ሁሉ ግዙፉ የሚባለው ነው። ከፍተኛውንም የበጀት ድርሻ በመያዝም ይንቀሳቀሳል። ተግባርና ሃላፊነቱ የዚያኑ ያህል ከባድ፣ ውስብስብና ለሰራዊታችን የውጊያ ብቃትና የድል የበላይነት እጅግ ወሳኝ ከመሆኑ አንፃር ግዝፈቱም ሆነ ከፍተኛውን የበጀት ድርሻ መያዙ ተገቢ ነው።

ወደመምሪያው ምድረግቢ ገብተን ተገቢው አቀባበል ከተደረግልን በኋላ ስለአጠቃላይ መምሪያው እንቅስቃሴ፣ ተግባርና ሃላፊነት እንዲሁም ዓላማና ግብ መግለጫ ይሰጡን ዘንድ ቆፍጣናውና ባለግርማ ሞገሱ ሜጀር ጀነራል ገዛኢ አበራ መድረኩን ተረከቡ። ሙሉ ለሙሉ አካዳሚያዊ መሰረት ያለው ገለፃቸውንም ጀመሩ። (ምንም እንኳን የሰጡን ገለፃ ጥልቅና ሰፊ ቢሆንም ለዚህ ፅሁፍ ይሆን ዘንድ በዚህ መልክ ቀርቧል።) ገለፃቸው በጥቂቱ የሚከተለውን መልዕክት በማዕከላዊነት የያዘ ነው።

ይህ የመከላከያ ሰራዊታችን የሎጀስቲክስ መምሪያ ራሱን የቻለ ዓላማ ያለውና በዲዛይን ማጎልበት፣ ማሻሻል፣ ማሰባሰብ፣ ማከማቸት፣ ማሰራጨት፣ ማጓጓዝና ፣ መንከባከብን መሰረት ባደረገ ፖሊሲ የሚመራ ግዙፍ ተቋም ነው። በሰራዊቱ አጠቃላይ እንቅስቃሴ ውስጥ ወሳኝ

የሆኑት (ከስልጠና እስከውጊያ፣ ከሰላማዊ እንቅስቃሴ እስከ ማህበረሰባዊ ልማትና ሰብአዊ ተግባራት፣ ከአመራር እስከ ውሳኔ አሰጣጥ፣ ከጦር መሳሪያ እስከ ዕህፈት መገልገያ፣ ከአልባሳት እስከ ምግብና መድህኒት አቅርቦት - - -) ያሉት ስራዎች የሚከናወኑትና በተገቢው ጊዜና ቦታ ለሰራዊቱ የሚመቻቹት በዚህ መምሪያ አማካኝነት ነው። በአጠቃላይ ሰራዊቱን በተጥቅና ስንቅ ሁሌም ዝግጁ አድርጎ ማቅረብ የመምሪያው ተቀዳሚ ኃላፊነት ነው።

ዘመቻዎችን ማደራጀት፣ 24 ሰአት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሰራዊቱን ከአንድ የውጊያ አውድ ወደ ሌላ የውጊያ አውድ ማንቀሳቀስ ከዚህ መምሪያ የሚጠበቅ ተግባር ነው። እነዚህ እንቅስቃሴዎች አንዱ ከሌላው ተነጥሎ አይታዩም፡፡ ሁሉም እንቅስቃሴዎች ተደጋጋፊና ሰራዊታችን ለሚያከናውናቸው ዘርፈ ብዙ ወታደራዊ ተግባራት የጀርባ አጥንት ናቸው።

መምሪያው ኃላፊነቱን የሚወጣው በመንግስት ከሚመደብለት በጀት በተጨማሪ ያለውን የውስጥ አቅም አሟጦ በመጠቀም ጭምር ነው፡፡ በዚህ ረገድ በመምሪያው የሚገኙት ኢትዮጰያውያን ወጣት ባለሙያዎች ያለሰለሰ ጥረት ትልቅ ስፍራ ይሰጠዋል። እዚህ ላይ መምሪያው በዚህ አቅሙ ምን ሰራ የሚል ጥያቄ መቅረቡ አይቀርም፡፡

በሎጂስቲክስ መምሪያው ስር ሌሎች ንኡሳን ክፍሎች ያሉ ሲሆን አንዱና ዋናው የሜንቴናንስ ክፍል ነው። ይህ ክፍል በርካታ ቁልፍና እጅግ አስገራሚ ተግባራትን የፈፀመና እየፈፀመ ይገኛል፡፡ ከነዚህም መካከል ከሃይል የወጡትን እንደ ዋዝ፣ ጋዝ፣ ኡራል የመሳሰሉትን ጨምሮ ለመካከለኛ አመራሮች የሚያገለግሉ አነስተኛ ተሽከርካሪዎችን፣ ታንኮችን፣ ከ30ና 40ዓመታት በፊት አልቆላቸዋል ተብለው የተጣሉ ከባድና ቀላል የውጊያና የትራንስፖርት ተሽከርካሪዎችን (ታንኮች፣ አየር መቃወሚያዎች ወዘተ.) ከየጫካው በማሰባሰብ አጠቃላይ ውስጣዊና አካላዊ እድሳቶችንና ጥገናዎችን ያከናውናል፡፡ ቀደም ሲል በቤንዚን ይሰሩ የነበሩ ተሽከርካሪዎችን የናፍታ አገልግሎት እንዲሰጡ ያደርጋል፡፡

በዚህም አማካኝነት የተሽከርካሪዎቹን አቅም እስከ 80 በመቶ በማሳደግ ለስራ ዝግጁ ያደርጋል፡፡ የጦር መሳሪያዎቹን የውጊያ ብቃትም በእጅጉ ያጎለብታል፡፡ ክፍሉ የሚያናውናቸው እነዚህ ተግባራት የውጭ ምንዛሪን ጨምሮ አጠቃላይ የአገሪቱን ወጪ በከፍተኛ ደረጃ ማዳን ችሏል፡፡ ለዚህ ተግባር ከ50 እስከ 60 ሺ ዩሮ ይጠይቅ የነበረውን ወጪ ከ90 እስከ 120 ሺ ብር ማውረድ መቻሉን ብ/ጀነራል ዘውዱ እሸቴ አብራርተዋል፡፡

ብርጋዴር ጀነራል ዘውዱ እንዳሉት በተያዘው ዓመት ብቻ ከፍሉ 50 ተሽከርካሪዎችን ጠግኖ ለአገልግሎት አብቅቷል፤ በአሁኑ ወቅት ደግሞ ሌሎች 400 ተሽከርካሪዎች ለአገልግሎት ዝግጁ እንዲሆኑ አድርጓል፡፡

የአገር መከላከያ ሚኒስቴር ካሉት ሰባት ተመሳሳይ ማዕከላት አንዱ የሆነው የጥገና ማዕከል እነዚህን ተግባራት የሚያከናውን በእቅድ ሲሆን 17 ትላልቅ ተሽከርካሪዎችን በማደስና በመጠገን ለወታደራዊ ግዳጅ ለማዘጋጀት የሚወስድበት ጊዜ በ18 ቀን ብቻ ነው፡፡
ማዕከሉ የሚያከናውናቸው ተግባራት ሁሉ የተባበሩት መንግስታት ድርጅትን ስታንዳርድ መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡ ይህም ሰራዊታችን ለሰላም ማስከበር ወታደራዊ ተግባር በሄደባቸው አገሮች ሁሉ ውጤታማ እንዲሆንና በሚመለከታቸው አህጉርና አለም አቀፍ ተቋማት - - - ተአማኒነትን፣ ክብርና ሞገስን እንዲጎናፀፍ አስችሎታል - የሎጂስቲክሱ ማዕከል።

በተከታዩ ቀን የጎበኘነው የቢሾፍቱ አቶሞቲቨ ኢንጂነሪንግ ማዕከል ነው። በቢሾፍቱ ከተማ የሚገኘው ይህ ማእከል የቴክኖሎጂ ሽግግርንና የሰው ሃይል ልማትን አቢይ ትኩረቱ አድርጎ የሚንቀሳቀስ አንዱ የሰራዊታችን ተቋም ነው። ይህ ተቋም የሰራዊቱን የተለያዩ መሳሪያዎች ከማጎልበት በተጨማሪ አገሪቱ በተያያዘችው የልማት ጎዳና ወስጥም የማይናቅ ሚና በመጫወት ላይ ይገኛል፡፡

ማእከሉ የሰራዊቱን ተሽከርካሪዎችና ታንኮችን ጨምሮ የኮንስትራክሽን መሳሪያዎችን፣ አውቶቡሶችን፣ ሚዲባሶችን፣ አውቶሞቢሎችንና ሌሎች አገሪቱ እያካሄደች ያለችውን ልማት የሚደግፉ የግንባታ ማሽኖችን (ዶዘሮችን፣ ኮሚዮኖችን፣ ሎቤዶችን ወዘተ) የመጠገን፣ የማደስና የመገጣጠም ስራዎችን ያከናውናል።

ማዕከሉ እነዚህን ተግባራት ለማከናወን ይቻለው ዘንድ በርካታ የሰለጠኑ ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎችን ያሰማራ ሲሆን የውጪ አገር የቴክኖሎጂ ስሪት የሆኑ ምርቶችን (መለዋወጫዎችንና ሞዴሎችን) ሙሉ ለሙሉ ወደ አገር ውስጥ በማስገባት፣ ስራ ላይ በማዋልና የቴክኖሎጂ ሽግግሩንና የሰው ኃይል ልማቱን በማፋጠን ላይ ይገኛል።

ማዕከሉ ስራውን ሙሉ በሙሉ ማለት በሚቻል ደረጃ በኢትዮጵያውያን ወጣቶች የሚያከናውን ሲሆን 50 በመቶ አካባቢ ሴቶች መሆናቸው ማዕከሉን ልዩ ያደርገዋል። በተለይም በቢሸፍቱ ከተማ የሚገኙ ከ52 በላይ አነስተኛና ጥቃቅን ተቋማትን በግብአትነት

መጠቀሙና በዘርፉ የተደራጁ ወጣቶቸን ተጠቃሚ ማድረጉ ልዩ ገፅታው ነው። ይህም መንግስት በስትራቴጂያዊ ዕቅዱ ለያዘውና ከአነስተኛና ጥቃቅን ማዕከላት የወደፊቶቹን ኢትዮጵያዊ ባለ ኢንዱስትሪዎች የማፍራት ዓላማ ዕውን መሆን ከወዲሁ መገመት ከባድ አይሆንም ።

የቢሾፍቱ አቶሞቲቨ ኢንጂነሪንግ ማዕከል የተለያዩ ፋብሪካዎች አሉት፡፡ የታንክ ማምረቻ ፋብሪካ (Tank Production Factory) በዋናነት ወታደራዊ ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎች የሚመረቱበትና በስሩም የተለያዩ የስራ ዓይነቶች ማለትም የማሻሻል፣ መገጣጠም፡ ኃይል መጨመርና የመሳሰሉት ይከናወኑበታል። ማዕከሉ ተሽከርካሪዎችን ወደኃይል ለመመለስ፣ ለገበያ ለማቅረብ፣ ለመገጣጠምና ደረጃቸውን የጠበቁ ለማድረግ ያስችለው ዘንድ ከውጪ ኩባንያዎች በግዢ የሚያስገባቸው ሞተርና ሻንሲ ብቻ ሲሆኑ ሌሎቹ ሙሉ በሙሉ በአገር ውስጥ በአገሪቱ ባለሙያዎች የሚፈበረኩ ምርቶችን ነው የሚጠቀመው።

በዚህ ተቋም ውስጥ በርካታ ተዘርዝረው የማያልቁ ተግባራት ቢኖሩም ከውጪ ተገዝተው የመጡ ተሽከርካሪዎችንና ታንኮችን ደረጃ የማሳደግ፣ ከአካባቢው የአየርና መልከዐምድር ሁኔታ አንፃር መልሶ የመስራት ፣ ፍጥነት የመጨመር (በሰዓት እስከ 80 km እንዲበሩ የማድረግ) ስራዎችና ለውጭ አገር በተለየም ለአፍሪካ አገራት የግዢ ጥያቄዎች እየሰጠ ያለው ምላሽ ሳይጠቀሱ የሚታለፉ አይደሉም።

ይህ ተስፋ ሰጪና ብርሃን ፈንጣቂ የመከላከያ ሰራዊታችን ቴክኖሎጂ ዕመርታ ከወታደራዊ ሃላፊነቱ ባሻገር ያለ አኩሪ ተግባር የሀገራችንን ህዳሴ በቅርብ ጊዜ ውስጥ እውን እንደሚያደርግ በዕርግጠኝነት መናገር የሚያስችለን ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

ወደ ኮንስትራክሽኑ ክፍል ስንመጣም የምናገኘው በተመሳሳይ መልኩ የቴክኖሎጂ ሽግግሩን በማጢጢፍ ላይ የሚገኙ የስራ ዘርፎችን ነው። ዘርፉ ከታወቁ የቻይና፣ ጣልያንና ሃይውንዳይ ካምፓኒዎች ጋር በጋራ የሚሰራ ሲሆን ራሱን ችሎ እየወጣና ወደ ትልቅ ፋብሪካነት እያደገ ያለ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

ሌላው Vertical Test በመባል የሚጠራው ክፍል ሲሆን ተግባሩም ቀደም ባሉት ክፍሎች የተሰሩትን ምርቶች በትክክል ስለመሰራታቸው ተገቢውን ምዘናና ክትትል የሚያደርግ ነው፡፡ ክፍሉ የምርቶቹን ውስጣዊና ውጫዊ ክፍሎች በሚገባ የሚመረምርና ጥራታቸውን የሚያረጋግጥ ክፍል ነው። ይህ ክፍል በትክክል የተሰሩትን ለሚቀጥለው የማጣሪያ ማእከል

(Inspection center) የሚያቀብል ሲሆን ማእከሉም በአሰራራቸው ያልተማመነባቸውን ከነችግሮቻቸው ወደኋላ በመመለስ እንደገና እንዲሰሩ ትእዛዝ ያስተላልፋል፡፡ የኢንስፔክሽን ክፍሉ ሌሎች በርካታ ሀላፊነቶች ያሉበት ሲሆን የጥራት ማረጋገጥ፣ የማማከር፣ ከደንበኞች ግብረመልስ (Feedback) መቀበል፣ በተገኙ ግብረመልሶች አማካይነት ችግሮችን መፍታትና ከደንበኞች ጋር ቅርብ ግንኙነት መፍጠር የዚህ ክፍል አበይት ተግባራት ናቸው።

ባጠቃላይ፣ ከላይ በአጭሩና በጥቅሉ የተመለከትናቸው ሁለት የመከላከያ ሰራዊታችን ተቋማት የሰራዊታችን ጠንካራ ክንዶች ሆነው በዘመናዊ አሰራር፣ በውጪ ቁጠባ፣ በቴክኖሎጂ ሽግግርና በሰው ኃይል ልማት ቁልፍ ሚና የሚጫወቱ ናቸው፡፡ ከዚህም ባሻገር በአምስት አመቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ስኬት ፈጣን ልማቱን በማስቀጠልና በሰራዊቱና በሲቪል ማህበረሰቡ መካከል ያለውን ድንበር በማዋሀድና የጋራ አመለካከትን በመፍጠር ረገድም አገራዊ ኃለፊነቱን በመወጣት ላይ መሆኑን በቀላሉ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህም ሌላ ጉብኝቴ የአገራችን መከላከያ ተቋም ከወታደራዊ ተቋምነቱ ባሻገር የዘመናዊ ቴክኖሎጂ ምንጭ፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ እውቀት ማእከል እንደዚሁም የኢኮኖሚ ልማት ኃይል እየሆነ መምጣቱን ተገንዝቤያለሁ፡፡

የሌሎቹን የመከላከያ ተቋማት ሁኔታ በሚቀጥለው ጽሁፌ ይዤ እንደምርብ ቃል እየገባሁ ይህንን በዚሁ አበቃሁ።